በአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት

መዋቅራችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማወያየት የተዘጋጀ አጭር ማስፈፀሚያ ዕቅድ

ታህሳስ **4/2014** ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

የብልፅግና ፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ህዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የተከፈተብንን ሁሉን አቀፍ ጦርነት ለመቀልበስ እስከአሁን የተደረገውን እንቅስቃሴ በመገምገም ቀጣይ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል። ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ኢትዮጵያን የማፍረስ ግብን ይዘው የሚንቀሳቀሱ የአገር ውስጥና የውጭ ጠላቶች በከፈቱብን ሁሉን አቀፍ ጦርነት ምክንያት የተደቀነብንን የህልውና አደጋ በፓርቲው በሳል አመራር፣ በፌዴራልና በክተማችን የፀጥታ ኃይሎች ጀግንነትና ውጤታማነት እና በሕዝቡ ሕብረብሔራዊ አንድነትና ርብርብ ለመቀልበስ እየተደረገ ያለው ጥረት አመርቂ መሆኑን ገምግሟል፤ ለፀጥታ ኃይሎችና ለሕዝቡም ምስጋና አቅርቧል። ይሁንና ቀጣይ ሥራዎች መሰራት እንዳለባቸውና መዘናጋት እንደሌለብን ታይቷል። ሌላዉ አሸባሪዉ ህወሓት እና ሸኔ የጦርነቱ ማብቅያ አዲስ አበባ እንደሆነ በመግለጽ ሲያደርጉት የነበረዉን ኢትዮጵያን

የማፍረስ ህልማቸዉን እንዳይሳካ መላዉ መዋቅራችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተቀናጅተዉ የአካባቢያቸዉን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ ረገድ አኩሪ ገድል መፈጸም ችሏል። ተጠናክሮ መቀጠልም ይኖርበታል።

በተያያዘም በሥራ አስፈፃሚው ስብሰባ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የገጠመንን ጦርነት በፍጥነት በመቀልበስ እንዴት አቅማችንና ዋንኛ ትኩረታችንን ከጦርነት ዋና ግባችን ወደ ሆነው ሁለንተናዊ ብልፅግና ማረጋገጥ እንመልስ የሚለው በሰፊው ተመክሮበታል።

በዚህ መሰረት አሁን ካለንበት ሁኔታ አስፈንጥሮ ወደምንፈልገው የብልጽግና ምዕራፍ የሚያሸጋግረን በአንድ በኩል ሉዓላዊነታችንን አስጠብቀንና ጠላቶቻችንም ደግመው ለጦርነት እንዳያስቡን እያደረግን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን ሰላምና ዴሞክራሲ የሚተክሉና የሚያጸኑ ስራዎችን መስራት ወሳኝ እንደሆነ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል። ይህንንም ሊናሳካ የምንችለው በሰላም ጎዳና መሆኑ ተሰምሮበታል። በመሆኑም የሰላም ጎዳና አቅጣጫዎች፣ ስልቶችና ዐበይት ተግባራት በሥራ አስፈፃሚው ተለይቷል፤ ለአፈፃፀሙም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች፣ አባላትና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲወያዩበትና የድርሻቸውን እንዲወጡ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ስለሆነም የብልፅግና ፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያስቀመጣቸው አቅጣጫዎች ላይ አመራሩን፣ አባሉና ሕዝቡን በማወያየት ተገቢውን ግንዛቤ ይዘው የድርሻቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ይህ የተግባር ማስፈጸሚያ እቅድ ተዘጋጅቷል።

1. የዕቅዱ አላማ

- ✓ በየደረጃው የሚገኙ መዋቅራችን እና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አቅጣጫዎች ላይ ግልጸኝነት በመፍጠር ኢትዮጵያን በዘላቂነት ለማዳን ወሳኝ ለሆነው ሁለንተናዊ ብልፅግና የማረጋገጥ ግባችን የድርሻቸውን እንዲወጡ ማስቻል ነው።

2. የእቅዱ ግብ

- ✓ የሰላም ጎዳና አቅጣጫዎች፣ ስልቶችና ዐበይት ተግባራት ላይ ለቀጣይ ተልዕኮ የሚያዘጋጅ ግንዛቤና መግባባት ይፈጠራል።
- ✓ በሁሉም አከባቢዎች የሰላም ጎዳና አቅጣጫዎች፣ ስልቶችና ዐበይት ተግባራት በውጤታማነት ተግባራዊ ሆነው በቀጣይ ምዕራፍ ለሚሰሩ የሰላምና የዶምክራሲ ባህል የመትከልና የማፅናት ሥራዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።

3. በሚደረጉ ውይይቶች እንዲደረሱ የሚጠበቁ ድምዳሜዎች

- ✓ በሀገራችን ላይ የተከፈተው ጦርነት የሕወሃት አሸባሪ ቡድን፣ ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ፀረ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶቻችን፣ እንዲሁም የሁለቱም የውስጥ ተላላኪ የሆኑ የሽብር ቡድኖች በአንድነት ተባብረው በወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚውና በዲፕሎማሲው ግንባሮች የከፈቱት ሀገር የማፍረስ ዘመቻ መሆኑን፣
- ✓ የአገር ውስጥና የውጭ ጠላቶች በከፈቱብን ሁሉን አቀፍ ጦርነት በአገራችን ላይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጉዳቶች መድረሳቸውን፣

- ✓ ኢትዮጵያን የማፍረስ ግብን ይዘው የሚንቀሳቀሱ የአገር ውስጥና የውጭ ጠላቶች በከፈቱብን ሁሉን አቀፍ ጦርነት ምክንያት የተደቀነብንን የህልውና አደጋ በመዋቅራችን እና በፀጥታ ኃይሎች ጀግንነትና ውጤታማነት እና በሕዝቡ ሕብረብሔራዊ አንድነትና ርብርብ ለመቀልበስ እየተደረገ ያለው ጥረት ውጤታማ መሆኑ፣
- ✓ እስከአሁን ባለው ሁኔታ የጠላቶቻችንን እኩይ ዓላማ በማክሸፍና ኢትዮጵያን በማዳን ረገድ ላስመዘገብነው ስኬት ሚስጥሩ ህብረብሔራዊ አንድነታችንን ጠብቀን በህብር በመንቀሳቀሳችን መሆኑ፣
- ✓ ነገር ግን የተከፈተብን ሁሉን አቀፍ ጦርነት ገና ያላለቀና ቀጣይ ርብርብና ትግል የሚጠይቅ በመሆኑ መዘናጋት እንደሌለብንና በተለያዩ ግንባሮች ትግላችንን አጠናክረን መቀጠል እንዳለብን፣
- ✓ በተለይም የጠላት ኃይል የሆኑት አሸባሪዉ ህወሓት እና የሸኔ ሃይሎች ከተማችን ዉስጥ መረጋጋ እንዳይኖር ሲያደርጉት የነበረዉ ሙከራ በመወቅራችንና በጸጥታ ኃይላችን ጥምረት ማምከን መቻላችንና ለአፍታም ቢሆን ሳንዘናጋ አጠናክረን መቀጠል እንዳለብን፤
- ✓ ጦርነቱ በተራዘመ ቁጥር ፈተናው በሁለም ረገድ በከፍተኛ ደረጃ እየጠነከረ እንደሚሄድና በሀገርና በሕዝብም ጉዳቱ እየከፋ እንደሚሄድ፣
- ✓ በመሆኑም በጠላት የተያዙ የአማራ አከባቢዎችን (አፋር አስቀድሞ ሙሉ በሙሉ ነፃ ወጥቷል) በአጭር ጊዜ ነፃ በማድረግ በሰላም ጎዳና ወደ ዋናው ሁለንተናዊ ብልፅግና የማረጋገጥ ግብ አቅማችናና ትኩረታችንን ማድረግ እንደሚኖርብን፣
- ✓ በተያያዘም በጠላት የተያዙ የአማራና የአፋር አከባቢዎችን በአጭር ጊዜ ነፃ ካደረግን ቡኃላ የትግራይ ሕዝብ ከችግሩ እንዲማር እድል የሚሰጥ እንዲሁም የመከላከያ ሠራዊታችን ለዋናው ሕገ መንግስታዊ ተልዕኮው በብቃት ለመዘጋጀት ለአቅም ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ የማድረግ አቅጣጫ መከተል አገራዊ ፋይዳው የላቀ መሆኑ፣
- ✓ የሀገር መከላከያ ሠራዊትን በሞራል፣ በሰው ኃይልና በልዩ ልዩ ግብዓቶች ማጠናከር ቀጣይነት ባለው መልኩ መሰራት ያለበት መሆኑና የተጀመረው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑ፣
- ✓ በየአከባቢው የሚገኙ ንፁሃን የትግራይ ተወላጆችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር ጠላትን ለማዳከምና ሀገራዊ አንድነት ለማጠናከር ጠቃሚ በመሆኑ ሁሉም የድርሻውን ማበርከት እንዳለበት፣
- ✓ ትግራዋይ ተወላጆችን በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ለማወያየት እየተደረገ ያለዉ ጅምር እንቅስቀቃሴ አጠናክሮ በማስቀጠል የተማችን ተጋሩ በሀገር ግንባታዉ ላይ ኃላፊነታቸዉን እንዲወጡ ማስቻል ተገቢ መሆኑንን፤
- ✓ አካታች አገራዊ ምክክር (Inclusive National Dialogue) ማድረግ በኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዳ፣ በዋና ዋና ጉዳዮች አገራዊ መግባባት ለመፍጠርና ለሕብረብሔራዊ አንድነታችን እጅግ በጣም ጠቃሚና ፈተናዎችን ሁሉ ተቋቁመን በፍጥነትና በጥንቃቄ ገለልተኛ በሆነ ተቋም አመቻችነት መጀመር ያለብን ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ፣

- ✓ አካታች አገራዊ ምክክሩ ለኢትዮጵያ ችግሮች ኢትዮጵያዊ መፍትሔ ለማበጀት የሚያግዝ እንዲሁም ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ምቹ መደላልደል የሚፈጥርና ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ፋይዳው የላቀ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን በሚገባ መወጣት እንዳለባቸው፣
- ✓ ለአካታች አገራዊ ምክክሩ የመልካም ፈቃድ በር እንዲከፍትና የፖለቲካ አየሩን በሰላምና ዕርቅ መንፈስ ለመለወጥ ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ወንጀሎች በሕግ ጥላ ስር ያሉ እስረኞችን ተቋማዊና ህጋዊ ስርዓቱን በጠበቀ አኳኃን መፍታት በጣም አስፈላጊ መሆኑን፣
- ✓ በሕግ ጥላ ስር ያሉ እስረኞች ይፈቱ ስንል በደረሰባቸው ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት ምክንያት ፍትህ የሚጠይቁ ዜጎች ጉዳይ ከግምት ሳይገባ ቀርቶ ሳይሆን እስረኞቹን መፍታቱ በአገራችን እየተካሄደ ላለው የፖለቲካ ሽግግር ውጤታማ ለማድረግና ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ካለው አገራዊ ፋይዳ አኳያ የታየ መሆኑና ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ የሚፈፀም መሆኑ፣
- ✓ የማንኛውም ጦርነት መቋጫ ፖለቲካዊ መፍትሔ መሆኑ በሰሜን የሀገራችን ክፍል የገጠመንን ጦርነት በፍጥነት ከቀለበሰን ቡኃላ መንግስት በቀረፀው አጀንዳና ቅድመ ሁኔታ መሰረት፣ ከትግራይ ኃይሎች ጋር ጦርነቱን በውይይት ማጠናቀቅ አስፈላጊ መሆኑን፣
- ✓ ጦርነቱን በመቀልበስ ወደ ውይይት መገባቱ፣ የመጨረሻው ሰላም በብረት ሳይሆን በውይይት ብቻ የሚገኝ መሆኑን የሚያሰረግጥ መሆኑን፣
- ✓ ጦርነቱን በውይይት ማጠናቀቅ በአገራችን ጉዳይ እጃቸውን ለማስገባት ያሰፈሰፉትን ኃይሎች ቅስም እንድንሰብር ይረዳል፣
- ✓ ከጠላት ነፃ የውጡ አካባቢዎችን የማረጋጋትና መልሶ የማቋቋም ስራዎችን በተቀናጀ አኳኋን በውጤታማነት በመስራት አካባቢው እንዲያገግምና ሕዝቡ ወደ መደበኛ የህይወት መስክ እንዲመለስ ለማድረግ የሁላችንም ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑ፣
- ✓ በጦርነት ተሳትፎ ስም ስርዓት አልበኝነት እንዳይነግስ እያንዳንዱን ጉዳይ ተቋማዊና ህጋዊ ስርዓትን በተከተለ መልኩ መፈፀምና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑ፣
- ✓ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራንና ሌሎች ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች በሰላም ጥረቱ ላይ ተገቢና አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ፣
- ✓ ሰርጎ ገቦችን፣ ህገ ወጥ የጦር ዝውውርንና የኢኮኖሚ አሻጥርን ቁጥጥር ማጠናከር እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ከመደበኛ ሥራዎች ጋር በማጣጣም በሁሉም አከባቢዎች በጥንቃቄና በትኩረት ተግባራዊ ማድረግ በሰላም ጎዳና ሁለንተናዊ ብልፅግና የማረጋገጥ ግባችን ላይ ትኩረት ለማድረግ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ ሁሉም ኃላፊነትና ግዴታውን መወጣት ያለበት መሆኑ የሚሉ ናቸው።

4. መከናወን ያለባቸው ዝርዝር ተግባራት

- ✓ በከተማ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ማስፈፀሚያ እቅድ ማዘጋጀት እና ኦሬንቴሽን መስጠት፣
- ✓ የከተማ ፣ የክ/ከተማ፣ የወረዳ አመራሮች እና የመላዉ አባላት መድረክ በማዘጋጀት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅጣጫዎች ላይ ግልጸኝነት መፍጠርና የተቆጠረ ተልዕኮ መስጠት፣
- ✓ የከተማ ቢሮ እና ሴክተር ተቋም ኃላፊዎች በስራቸዉ የሚገኙ ሰራተኞቻቸዉ፣ አባላቶቻቸዉና ባለድርሻ አካላትን የማወያየትና ስምሪት የመስጠት ስራ በይሰራሉ፤
- ✓ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በውይይት መደረኮች ላይ መሳተፍ የሚገባቸው ተጽእኖ ፈጣሪዎችን መለየት፣
- ✓ የምሁራን ውይይት መድረክ በከተማ ደረጃ በማዘጋጀት ግልፀኝነትና መግባባት ሚፈጠር ሆኖ ተግባሩን በተዋረድ ባሉ ተቋማትም ሚቀጠል ይሆናል፤
- ✓ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ውይይት መድረክ በከተማ ደረጃ በማዘጋጀት ግልፀኝነትና መግባባት በመፍጠር በተመሳሳይ መልኩ በየደረጃዉ ሚካሄድ ይሆናል።
- ✓ የወጣቶች፣ ሴቶች፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ አርሶ አደሮችና ሌሎች ተጽእኖ ፈጣሪዎችን በክ/ከተማ አስተዳደር እና በወረዳ ደረጃ በማወያየት ግልፀኝነትና መግባባት መፍጠር፣
- ✓ ለተግባሩ አፈፃፀም ወጤታማነት ተከታታይ የሆነ የድጋፍና ክትትል ስራ መስራት፣

5. የእቅዱ ማስፈፀሚያ ስልት

- ✓ የውይይት መድረኮችን በአግባቡ ሊመሩ የሚችሉ አመራሮችን በመለየት ማሰማራት ያስፈልጋል፣
- ✓ ውጤታማ የውይይት መድረኮች በማመቻቸትና በብስለት በመምራት በሥራ አፈፃሚ ከኮሚቴው አቅጣጫዎቹ ላይ መግባባትና በተልዕኮዎቹ ላይ መተማመን መፍጠር ይኖርብናል።
- ✓ ሁሉም አመራሮችና አባላት ጉዳዩን በባለቤትነት ስሜት እንዲይዙት የማድረግ ስልት መከተል ያስፈልጋል።
- ✓ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጽእኖ ፈጣሪዎችን በመለየት በውይይት መድረኮች ላይ ማሳተፍ ያስፈልጋል።
- ✓ ጠንካራና ተቋማዊ የሆነ የድጋፍና ክትትል ግብረ ኃይል በማቋቋም አጠቃላይ አፈጻጸሙን እየገመገሙ መምራት ያስፈልጋል።

6. ድጋፍና ክትትል

- ✓ በከተማ ደረጃ የድጋፍና ክትትል ግብረ ኃይል በማቋቋም በሁሉም መደርኮች እንዲሰማሩ ማድረግ
- ✓ በየደረጃዉ ከሚገኙ የፓርቲ እና የአስተባባሪ ኮሚቴ አመራሮች ጋር የእለት ተእለት ግንኙነት በማድረግ የውይይት መድረኩን አፈጻጸም ይከታተላል።
- ✓ በየደረጃዉ ከሚገኙ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ጋር የእለት ተእለት ግንኙነት በማድረግ የመድረኩን አፈጻጸም ይከታተላል።

7. የሪፖርት ግንኙነት

- ✓ በከተማ ማዕከል ደረጃ በየቀኑ ሪፖርት ይቀበላል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል።
- ✓ በየደረጃዉ የሚገኙ የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በየቀኑ የስልክ/የመልዕክት ሪፖርት ያደረጋል። እንደአስፈላጊነቱ የጽሁፍ ሪፖርት ተጠቃሎ ይቀርባል።
- ✓ በሁሉም መድረኮች የተነሱ ሀሳቦች፣ ጥያቄዎች፣ ያከራከሩ ነጥቦችና ወጣ ያሉ እንግዳ ዝንባሌዎች (ካጋጠሙ) ተሰባስበው ለከተማ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት በጽሁፍ እንዲደርሱ መደረግ አለበት።
- ✓ ውይይቶቹ በመርሃ ግብሩ መሰረት ከተጠቃለሉ በኃላም በከተማ ደረጃ የአመራር፣ አባላትና የሕዝብ ውይይት መድረኮች አፈፃፀም በተመለከተ የተሳታፊዎች መረጃ፣ በአዎንታም ሆነ በአሉታ የተነሱ አንኳር አንኳር ጉዳዮች፣ የተደረሱ ድምዳሜዎችና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን የያዘ የተጠቃለለ ሪፖርት በማዘጋጀት ለከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት መላክ ይኖርበታል።

8. የድርጊት መርሃ-ግብር

- ✓ በከተማ ደረጃ ማስፈፀሚያ እቅድ ማዘጋጀትና ኦሬንቴሽን መስጠት - እስከ ታህሳስ 05/2014
- ✓ በየደረጃዉ ለሚገኘዉ አመራሮች ግልጸኝነት መፍጠርና የተቆጠረ ተልዕኮ መስጠት - እስከ ታህሳስ 08/2014
- ✓ ለፓርቲ አባላት ግልጸኝነት መፍጠርና የተቆጠረ ተልዕኮ መስጠት - እስከ ታህሳስ 09/2014
- ✓ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማወያየት ግልጸኝነት መፍጠር - እስከ ታህሳስ 10/2014
- ✓ የውይይቶች የተጠቃለለ ሪፖርት ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት መላክ - ታህሳስ 11/2014

ተ.ቁ	የዉይይት መድረክቹ ዓይነት	ሚፈጸምበት ግዜ	መድረኩ ሚካሄድበት ደረጃ	ለአወያይነት የተመደቡ አመራሮች
1.	የከተማዉ ከፍተኛ አመራሮች ኦሬንቴሽን መድረክ ✓ የከተማ ቢሮ ኃላፊች እና በቢሮ ደረጃ ያሉ ም/ቢሮ ኃላፊዎች ✓ በቢሮ ደረጃ ያሉ የከተማ አማካሪዎች ✓ የተቋማት ኃላፊዎች ✓ ሴክተር ልዩ ወረዳ ኃላፊዎች ✓ የክ/ከተማ አስተባባሪ ኮሚቴዎች	6/4/2014 ዓ.ም	በማዕከል	1.ክብርት ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አበቤ 2..ክቡር አቶ ጃንጥራር አባይ 3. ክቡር አቶ ጥራቱ በየነ
2.	የከተማ ቀሪ አመራሮች መድረክ	ታህሳስ 7/2014 ዓ.ም	በማዕከል	1.አቶ ጥራቱ በየነ 2.ወ/ሮ ሂክማ ከሂረይዲን
3.	መምህራን **(500** ተሳታፊዎች**)**	ታህሳስ 7/2014 ዓ.ም	በማዕከል	1.ክቡር ጃንጥራር አባይ 2.አቶ ዘላለም ሙላቱ 3.ዶ/ር ብርሃነመስቀል
4.	የሚድያ አካላት እና የኪነ ጥበበ ባለሙያዎች	ታህሳስ 7/2014	በማዕከል	1.ክብርት ከንቲባ አዳነች አበቤ 2.አቶ ተተካ በቀለ 3.ዶ/ር ሂሩት ካሳዉ
5.	የመህራን መድረክ **(300** ታሳታፊዎች**)**	ታህሳስ 8/2014 ዓ.ም	በማዕከል	1.ክቡር ጃንጥራር አባይ 2.ዶ/ር ብርሃነመስቀል 3.አቶ ዘላለም ሙላቱ
6.	የህገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች መደፍረክ	ታህሳስፐ 8/2014 ዓ.ም	በማዕከል	1.ክብርት ከንቲባ አዳነች አበቤ 2 ዶ/ር ቀነአ ያደተ 3.ወ/ሮ ያስሚን ወሃረቢ

7. 9	የንግዱ ማህበረሰብ አካላት**(300** ተሳታፊዎች**)**	ታህሳስ 9/2014 ዓ.ም	በማዕከል	1.ክብርት ከንቲባ አዳነች አበቤ 2.ክቡር አቶ ጥራቱ በየነ 3.ክብርት ወ/ሮ ነጂባ አክመል 4. ክቡር ግርማ ሰይፉ
	በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ የሚካሄዱ መድረኮች			
i.	የክ/ከተማ ጠቅላላ አመራርና የወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ መድረክ	ታህሳስ 7/2014 ዓ.ም		1.የክ/ከተማ ዋ/ ስራ አስፈጻሚ 2.የክ/ከተማ ፓርቲ ኃላፊ 3.ከከተማ ሴክተር አመራሮች በየክ/ከተማዉ 2 አመራር ሚመደብ ይሆናል
2.	የወረዳ ጠቅላላ አመራር መድረክ	ታህሳስ 8/2014 ዓ.ም	በወረዳ ደረጃ	1.የወረዳ ዋና አመራሮችና 2.በክ/ከተማ ሚመደቡ ደጋፊ አመራሮች
4.	የመ/ድርጅት እና የህዋሳት አመራሮች መድረክ	ታህሳስ 9/2014 ዓ.ም (ጠዋት ለግማሽ ቀን)	በወረዳ ደረጃ	በወረዳዉ በሚመደቡ አመራሮች
5.	የመላዉ አባላት መድረክ	ታህሳስ 9/2014 ዓ.ም (ከሰአት ለግማሽ ቀን)	በወረዳ ደረጃ	በወረዳዉ በሚመደቡ አመራሮች
6.	የሱቪል ሰርቪስ ሰራተኞች መድረክ	ታህሳስ 10/2014 ዓ.ም	በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ	በክ/ከተማዉ ዋና አመራሮች
7.	የነጋዴ ማህበረሰብ መድረክ	ታህሳስ 10/2014 ዓ.ም	በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ	በክ/ከተማዉ ዋና አመራሮች
8.	የመምህራን መድረክ	ታህሳስ 10/2014 ዓ.ም	በክ/ከተማ	በክ/ከተማዉ ዋና አመራሮች
9.	የአርሶ አደሮች መድረክ	ታህሳስ 10/2014 ዓ.ም	በክ/ከተማ	በክ/ከተማዉ ዋና አመራሮች
10. 10	የወጣቶች፣ ሴቶች የነዋሪዎች የአርሶ አደሮች እና የተጽዕኖ ፈጣሪዎች መድረክ <u>በየራሳቸዉ</u> ሚደረግ ይሆናል።	ታህሳስ 9/2014 ዓ.ም	በየደረጃዉ	በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ

- ✓ በከተማ ደረጃ ተግባሩን የሚያስተባብሩ አካላት
  1. አለማየሁ እጅጉ
  2. ደገፋ ገ/መድህን
  3. ተሻለ አክሊሉ ሲሆኑ
- ✓ በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ የሪፖርት፣ የመረጃ እና የግብረ መልስ ግብረ ኃይል በተመሳሳይ ሁኔታ የሚደራጅ ሆኖ የተግባሩ አፈጻጸም ለከተማ ማዕከል ሪፖርት ሚደረግ ይሆናል

<u>በአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ፅ/ቤት በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ከማዕከል እስከ ወረዳ በሚደረጉ የተለያዩ መድረኮች ለድጋፍ ክፍለ ከተማ የተመደቡ ደጋፊ አመራሮች</u>

ተ.ቁ	ክፍለ ከተማ	የተመደበ ደጋፊ አመራር	ሀላፊነት	ምርመራ
1	ቂርቆስ ክፍለ ከተማ	አቶ ኃይሉ ሉሌ	ፕፕሊክ ቢሮ የሪፎርም ዘረፍ ኃላፊ	
		ወ/ሮ ወይንሸት ዘሪሁን	ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት	
2	ልደታ	አቶ ግርማ ቤካ	የመልካም አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ	
		አቶ ጥላሁን ከበደ	በቢሮ ሀላፊ ደረጃ ቤቶች ምክትል	
3	ንፋስ ስልክ ላፍቶ	አቶ ጥላሁን ወርቁ	ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ	
		ኢ/ር ስጦታዉ አየለ	ማንባታ ፍቃድ ባለስልጣን	
4	ቦሌ ክፍለ ከተማ	ዶ/ር ዳዲ ወዳጆ	ፕላን ኮሚሽን	
		አቶ ብርሃኑ ኤካታ	አማካሪ	
5	ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ	አቶ አብረሃም ታደሰ	ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ	
		አቶ አስፋዉ ተክሌ		
6	የካ ክፍለ ከተማ	አቶ አስፋዉ ለገሰ	ህብረተሰብ ተሳትፎ	
		እናት አለም መለሰ	ትረስት ፈንድ	
7	ኮልፌ ክፍለ ከተማ	አቶ ጀማል አልዩ	መሬት ማኔጅመነት	
		አቶ ግርማ ወርቁ	ፓርቲ ጽ/ቤት	
8	አራዳ ክፍለ ከተማ	አቶ አስራት ንጉሴ	ምገባ ም/ኤጂንሲ	
		አቶ ጳዉሎስ ኩሳ	ም/ከንቲባ አማካሪ	
9	አቃቂ ክፍለ ከተማ	አቶ ዮሀንስ ምትኩ	ጥቃን ም/ቢሮ ኃላፊ	
		አቶ ዋቻሞ	ኮምንኬሽን መክትል	
10	አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ	አቶ መስፍን መንግስቱ	ትራንስፖርት ባለስልጣን	
		አቶ ሰለሞን ፍስሀ	እሳትና አደጋ ኮሚሽን ኮሚሽነር	
11	ጉለሌ ክፍለ ከተማ	አቶ ሲሳይ ጌታቸዉ	አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን	
		ወ/ት አንቺነሽ ተስፋዬ	ምገባ አጂንሲ	

ከጦርነት ወደ ብልፅግና - በሰላም ጎዳና በሚል ርዕስ በየደረጃው የተደረገውን የውይይት አፈጻጸም ለመላክ የተዘጋጀ የሪፖርት ማቅረብያ ነጥቦች

የሪፖርት ቀን፡----------

1. የውይይት/መድረክ ቅድመ ዝግጅት

✓ በጥንካሬና በድክ

✓ በድክመት

---

2. የተሳታፊዎች ዓይነት የተሳትፎ አፈጻጸም

ተ.ቁ	የመድረክ ዓይነት/ በመድረኩ የተሳተፉ አካላት	(ዕቅድ)			(ክንውን)			አፈጻጸም በመቶኛ	አስተያየት
		ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ		

3. በየመድረኩ የተነሱ ዋናዋና ሃሳቦች

✓ በጥንካሬ

✓ በድክመት

---

4. ከመወያያ ሰነዱ አውድ ወጣ ያለ ሀሳብ የተራመደባቸው መድረኮችና ሀሳቦች

---

5. በየደረጃው የተካሄዱ መድረኮች በተሳታፊዎች የታዩ አዝማምያዎች

✓ በጥንካሬ

✓ በድክመት

---

6. መግባባት ላይ የተደረሰባቸው ነጥቦች

---

7. በቂ ምላሽ/ማብራሪያ አላገኙም ተብለው የሚታሰቡ ነጥቦች/ሀሳቦች/ጥያቄዎች

---

8. በቀጣይ የብልጽግና ጉዟችን ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ተብለው ተብለው የተነሱ ሀሳቦች

ሪፖርቱን ያዘጋጀው አመራር ስም፡----------

ኃላፊነት ፡----------

ፊርማ ፡----------

ቀን ፡----------

ሰላም ለኢትዮጵያ፤ ሁለንተናዊ ብልጽግና ለሕዝባችን!!!!